## የሴት ልጆችን ብልት መግረዝ ህገወጥ ድርጊት ነው።

- የዩናይትድ ስቴትስ ፌዴራል ሕግ አንቀጽ 18 ኮድ § 116፣ ከ18 ዓመት በታች በሆኑ ሴቶች ላይ የብልት ግርዛት መፈጸም፤ ለመፈጸም ሙከራ ማድረግ፤ወይም ለማከናወን ማሴር፤ እንዲሁም ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሴቶችን ለግርዘት ዓላማ ከአካባቢ፣ከክልል፣ ወይም ከሃገር ውጭ ማጓጓዝን ይከለክላል።
- የሴት ልጅ ግርዛትን ከሃይማኖት ፣ከባህል፣ ከአምልኮ ስርዓት፣ ወይም ከተለምዶ ጋር አገናኝቶ ለማከናወን የሚያስችል የተለየ ሁኔታም የለም።
- ማናቸውም በሴት ብልት ግርዛት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የሚገኝ ሰው እስከ አስር አመት የሚደርስ እስራት ሊፈረድበት ይችላል።

> ***"ኤፍቢአይ፤ የወጣት እና ህጻን ሴት ልጆችን መብት ለማስጠበቅ ጽኑ አቋም ያለውና ይህንን መብት በሚጥሱ ላይም ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ በቁርጠኝነት ይሰራል።"***
>
> — የህዝባዊ ሙስናና የሰብአዊ መብቶች መምሪያ ኃላፊ

## ምንድንነው ሪፖርት የሚደረገው?

- እርስዎ ወይም የሚያውቁት ሌላ ሰው ለብልት ግርዛት አደጋ የተጋለጣችሁ ወይም የተከናወነባችሁ ከሆነ፤
- በአሜሪካ ውስጥ የሴትን ብልት ግርዘት ስለሚያከናውን ሰው መረጃ ካለዎት፤ ወይም
- ከአሜሪካ ውጭ ቢወሰዱ ለብልት ግርዛት ሊጋለጡ የሚችሉ ግለሰቦችን ያውቁ ከሆነ።

## እንዴት ሪፖርት ማድረግ ይቻላል?

**የኤፍቢአይ የጥቆማ መስመር:** 1-800-CALL-FBI 1-800-225-5324

**በድረገጽ:** **tips.fbi.gov**

**ወይም <u>በአካባዎ ያለውን የኤፍቢአይ የመስክ ቢሮ</u> ፣ ወይም <u>በቅርብ የሚገኘውን የአለም አቀፍ ቢሮ</u> ያግኙ።**

## ጥያቄዎች ቢኖሩዎት ወይም መረጃ ቢፈልጉ

የጤናና ሰብአዊ አገልግሎት፤ የሴቶች ጤና ጉዳይ ቢሮ የድጋፍ መስመር በ1-800-994-9662 ይደውሉ
ወይም

የህጻናት ድጋፍ- ብሄራዊ የህጻናት ጥቃት የቀጥታ መስመር 1-800-4-A-CHILD (1-800-422-4453) ይደውሉ

**የፍትህ ሚኒስቴር**
የፌዴራል ምርመራ ቢሮ




# የሴት ልጆችን ብልት መግረዝ ይቁም (FGM)

# የሴት ልጆችን ብልት መግረዝ

- ✓ የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው
- ✓ በሴት ልጆች ላይ የሚፈጸም በደል ነው
- ✓ የጾታ አድልዎ ነው
- ✓ በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ የሚፈጸም አመጽ ነው

## የሴትን ብልት መግረዝ ማለት ምንድን ነው?

ይህ መቁረጥ፤ግርዘት፤ የማንጻት ስራ ወይም የሴቶችን ብልት መተልተል (ኤፍጂኤም) ተብሎ የሚጠቀስ ድርጊት ፣ የሴትን ብልት ውጪያዊ አካል በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ማስወገድን ወይም፤ ለሕክምና አስፈላጊ ባልሆነ ምክንያት፤ በሴት ልጆች ብልት ላይ የሚደርሱ ሌሎች ጉዳቶችን ያካትታል። አድራጎቱም፤በመውጋት፤ በመቁረጥ፤በጋለ ነገር በመተኮስ፤ወይም በመፈቅፈቅ የውጭውን እና የውስጥ የብልት ከንፈርን ከማስወገድ፤ ለሽንትና ለወር አበባ የሚሆን ትንሽ ክፍተት ብቻ በመተው፤ የሴቷን ብልት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ እስከመስፋት ድረስ ሊዘልቅ ይችላል።

## በማን ላይ ይከናወናል?

የሴትን ብልት መግረዝ በአብዛኛው የሚከናወነው ከህጻንነት እስከ 15 አመት በሆኑ ወጣት ልጃገረዶች ላይ ሲሆን፤ አልፎ አልፎም ልክ ከጋብቻ በፊት ይከናወናል። ድርጊቱም፣ በባህላዊ ባለሙያዎች ወይም በዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች ሊከናወን ይችላል።

## ለምን ይከናወናል?

የሴትን ብልት መግረዝ ባህላዊ ልምድ እንጂ ሀይማኖታዊ ሥርዓት አይደለም።
አንዳንድ የማህበረሰብ አባላት፤ የሴት ልጆችን ብልት መግረዝ በሃይማኖት የታዘዘ እንደሆነ ያምናሉ። የሴት ብልት ግርዛትን የሚፈጽሙ ማህበረሰቦች፣ ድርጊቱ የሴት ልጅን ተገቢ አስተዳደግ እንደሚያረጋግጥ፣ የቤተሰብን ክብር እንደሚያስጠብቅና/ወይም ሴት ልጅን ለጋብቻ ተስማሚ እንደሚያደርጋት ያምናሉ። የሴትን ብልት መተልተል፣ በአንዳንድ ባህሎች ውስጥ በጥልቀት ስር የሰደደ ከመሆኑ የተነሳ በአንድ ጎሳ ወይም በአንድ ሃይማኖት ብቻ ተወስኖ የሚከናወን ድርጊት ወይም ልምድ አይደለም።

## የጤንነት ጠቀሜታ የለውም — ወደ ሞት ሊመራ ይችላል

የሴትን ብልት መግረዝ ምንም ዓይነት የጤና ጠቀሜታ የሌለው፣ ከባድ አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ነው።ድርጊቱ በሚፈጸም ወቅት ከሚከሰት ከባድ ሕመም አንስቶ እስከ የደም መፍሰስ፣ የመሽናት ችግር፣ የመመረዝ፣ እና እስከ ሞት ሊያደርስ ይችላል። በረጂም ጊዜ ደግሞ፤ ከመሽናት፣ ከብልት፣ ከወር አበባ፣ ከወሲብ እና ከወሊድ ጋር የተዛመዱ ችግሮችን ሊያስከትልና በተጨማሪም በአራስ ህጻናት ላይ ሊደርስ የሚችል የላቀ የሞት አደጋን ተከትሎ የሚመጣ የስነልቦናዊ ችግር ሊያስከትል ይችላል።

***በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ቢያንስ 513,000 ሴቶች እና ልጃገረዶች ለብልት መገረዝ አደጋ ተጋልጠዋል ወይም አስቀድሞ ተከናውኖባቸዋል።***

— የበሽታ መቆጣጠሪያና መከላከያ ማእከል 2016

## የሴቶችን ብልት መግረዝ በ92 አገራት ውስጥ በሰፊው ይፈጸማል

የሴትን ብልት መግረዝ ፤ በአለም ዙሪያ በበርካታ አገሮች በአፍሪካ፣ በኤዢያ፣ በመከከለኛው ምስራቅ፣ በደቡብ አሜሪካ፣በአውሮፓ እና እንዲሁም በሰሜን አሜሪካ፤ በአገሬው ተወላጆችና በዳያስፖራ ህብረተሰብ መካከል ይከናወናል።




## ሴት ልጅ ለብልት መገረዝ አደጋ የተጋለጠች መሆኗን የሚጠቁሙ ምልክቶች:

- "ቆራጭ" በመባል የሚታወቅ ዘመድ ወይም ሌላ ሰው ከውጭ አገር ለጉብኝት መምጣት፣
- አንዷት ልጅ ‘ለአቅመ ሔዋን ‘ ወይም ‘ለጋብቻ የደረሰች’ ' ከመሆኗ ጋር ተያይዞ የልዩ አጋጣሚ ዝግጅት ወይም ስነ ስርአት የሚደረግ ከሆነ፣
- እንደ እናት፣ እህት፣ ወይም አክስት የመሳሰሉ የሴቴ ዘመዶች ላይ የብልት መገረዝ የተከናወነባቸው ከሆነ፣.
- አንድ ቤተሰብ፣ ባህር ማዶ የሚገኙ ዘመዶቻቸውን ለመጎብኘት በበጋው ወቅት የሽርሽር እቅድ እያዘጋጁ ከሆነ፣
- አንዷት ልጅ፣ ባልተጠበቀ መልኩ ወይም ረዘም ላለ ጊዜ ከትምህርት ቤት ርቃ የቆየች ከሆነ፣
- አንዷት ሴት ልጅ፣ ትምህርቷን ለመቀጠል መቸገር።
- አንዷት ልጅ ከቤቷ የኮበለለች መሆኗ ወይም ለማምለጥ እቅድ የምታወጣ ከሆነ ናቸው።

## የሴት ልጅ የብልት ግርዘት አስቀድሞ ተከናውኖ እንደሆነ የሚጠቁሙ አመልካቾች:

- ለመራመድ፣ ለመቆም፣ ወይም ለመቀመጥ መቸገር፣
- በመታጠቢያ ወይም በመጸዳጃ ቤት ረዘም ያለ ጊዜ ማሳለፍ፣
- በእግሮቻቸው መካከል ስለሚኖር ህመም ማጉረምረም፣
- ጸጥ የማለት፣ የመከፋትና የመንፈስ ጭንቀት ገጽታ ማሳየት፣
- ከትምህርት ቤት ወይም ከኮሌጅ ከመቅረት በኋላ በተለየ ባህርይ እና ተግባር መጠመድ፣
- ወደ ሀኪሞች ለመሄድ ወይም የህክምና ምርመራ ለማድረግ ማንገራገር፣
- የሆነ ሰው በነርሱ ላይ ስላደረገው ነገር ሊገልጹት ያልተፈቀደላቸው ነገር እንዳለ ማውራት፣
- እርዳታ ይጥይቃሉ፤ ሆኖም ግን፣ ከመፍራት ወይም ከማፈር የተነሳ ችግሩን በግልጽ ለመናገር መቸገርን ያካትታሉ።